ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Civil Service Commission

ቁጥር/Ref.No. ቁጥር ሲ.ሰኮ30/ጠ10/1/17

ቀን/Date ጥቅምት 1 ቀን 2017 ዓ.ም

ለዝርዝራቸው ከዚህ ጋር ለተያያዘ መሥሪያ ቤቶች

አዲስ አበባ

መንግሥት ሠራተኞች በተለይ በዝቅተኛ ደመወዝ ተከፋይ ሠራተኞች ላይ የደረሰውን የኑሮ ውድነት በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ ከጥቅምት 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ ለመንግሥት ሠራተኞች፣ ለመንግሥት ተሿሚዎች እና ለህዝብ ተመራጮች የደመወዝ ማሻሻያ እንዲደረግ መወሰኑን የገንዘብ ሚኒስቴር መስከረም 29 ቀን 2017 በቁጥር በሠ2/6/6 በተጻፈ ደብዳቤ ገልጾልናል፡፡

ውሳኔውን ለማስፈጸም የተዘጋጀው የደመወዝ ማስተካከያ መመሪያ በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የኮሚሽነሮች ጉባኤ አባላት ታይቶ ከጥቅምት 1 ቀን 2017 ዓ.ም ጀምሮ የጸደቀ ሲሆን፣ ለፍትህ ሚኒስቴር ተልኮ ወመመሪያ ቁጥር 1029/2017 ተብሎ የተመዘገበና በሚኒስቴሩ ድረ-ገጽ መጫኑን አስታውቆናል፡፡

በዙሁ መሠረት የመንግሥት ሠራተኞችን የደመወዝ ማስተካከያ ለማስፈጸም የተዘጋጀውን፣

1. የመንግሥት ሠራተኞች ደመወዝ ስኬል ሠንጠረዥ፣
2. የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ ሠንጠረዥ እና
3. የደመወዝ ማስተካከያ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1029/2017፣

ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን መላካችንን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

ግልባጭ

ለኮሚሽነር ጽ/ቤት
ለም/ኮሚሽነር ጽ/ቤት
ለክፍያና ጥቅማ-ጥቅም መሪ ሥራ አስፈጻሚ
ለአደረጃጀትና ሥራ ምዘና መሪ ሥራ አስፈጻሚ
ለኢንስፔክሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ
ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን

ስልክ/Tel +251 11 554 96 66
011 554 96 67
011 554 96 68
ፋክስ/Fax +251 11 554 97 07
+251 11 554 96 63
ፖ.ሳ.ቁ/Po.box-1082
ኢሜል/Email-ethiocs@gmail.com
ዌብ ሳይት/website-www.csc.gov.et

አዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ 09 ከፍላሚንጎ ሬስቶራንት 100 ሜትር ገባ ብሎ
ማገልገል ክብር ነው!

# ሠንጠረዥ-1
## የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል
## (ጥቅምት 2017 ዓ.ም)

| ደረጃ | መነሻ ደመወዝ | የእርከን ደመወዝ | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| I. | 4760 | 4929 | 5104 | 5283 | 5467 | 5659 | 5855 | 6058 | 6269 | 6485 | 6709 |
| II. | 4929 | 5104 | 5283 | 5467 | 5659 | 5855 | 6058 | 6269 | 6485 | 6709 | 6940 |
| III. | 5104 | 5283 | 5467 | 5659 | 5855 | 6058 | 6269 | 6485 | 6709 | 6940 | 7180 |
| IV. | 5283 | 5467 | 5659 | 5855 | 6058 | 6269 | 6485 | 6709 | 6940 | 7180 | 7424 |
| V. | 5659 | 5855 | 6058 | 6269 | 6485 | 6709 | 6940 | 7180 | 7424 | 7676 | 7934 |
| VI. | 6058 | 6269 | 6485 | 6709 | 6940 | 7180 | 7424 | 7676 | 7934 | 8199 | 8474 |
| VII. | 6485 | 6709 | 6940 | 7180 | 7424 | 7676 | 7934 | 8199 | 8474 | 8758 | 9047 |
| VIII. | 6940 | 7180 | 7424 | 7676 | 7934 | 8199 | 8474 | 8758 | 9047 | 9341 | 9645 |
| IX. | 7424 | 7676 | 7934 | 8199 | 8474 | 8758 | 9047 | 9341 | 9645 | 9953 | 10272 |
| X. | 7934 | 8199 | 8474 | 8758 | 9047 | 9341 | 9645 | 9953 | 10272 | 10600 | 10934 |
| XI. | 8474 | 8758 | 9047 | 9341 | 9645 | 9953 | 10272 | 10600 | 10934 | 11279 | 11634 |
| XII. | 9047 | 9341 | 9645 | 9953 | 10272 | 10600 | 10934 | 11279 | 11634 | 12001 | 12379 |
| XIII. | 9645 | 9953 | 10272 | 10600 | 10934 | 11279 | 11634 | 12001 | 12379 | 12765 | 13163 |
| XIV. | 10600 | 10934 | 11279 | 11634 | 12001 | 12379 | 12765 | 13163 | 13574 | 13995 | 14429 |
| XV. | 11634 | 12001 | 12379 | 12765 | 13163 | 13574 | 13998 | 14432 | 14879 | 15340 | 15802 |
| XVI. | 12765 | 13163 | 13574 | 13998 | 14432 | 14879 | 15340 | 15802 | 16267 | 16738 | 17220 |
| XVII. | 13998 | 14432 | 14879 | 15340 | 15802 | 16267 | 16738 | 17220 | 17716 | 18226 | 18751 |
| XVIII. | 15340 | 15802 | 16267 | 16738 | 17220 | 17716 | 18226 | 18751 | 19291 | 19820 | 20363 |
| XIX. | 16738 | 17220 | 17716 | 18226 | 18751 | 19291 | 19820 | 20363 | 20921 | 21491 | 22072 |
| XX. | 18226 | 18751 | 19291 | 19820 | 20363 | 20921 | 21491 | 22072 | 22652 | 23232 | 23813 |
| XXI. | 19820 | 20363 | 20921 | 21491 | 22072 | 22652 | 23232 | 23813 | 24397 | 24982 | 25567 |
| XXII. | 21491 | 22072 | 22652 | 23232 | 23813 | 24397 | 24982 | 25567 | 25622 | 26288 | 26959 |

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

# ሠንጠረዥ-2
# የመንግሥት ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል የመሸጋገሪያ ሠንጠረዥ
## ጥቅምት 2017ዓ.ም

| ደረጃ | መግለጫ | መነሻ ደመወዝ | የእርከን ደመወዝ | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| I | አዲስ ደመወዝ | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 | 4760 |
| | ነባር ደመወዝ | 1100 | 1174 | 1253 | 1338 | 1428 | 1523 | 1624 | 1731 | 1843 | 1958 | 2079 |
| | | | | | | | | | | | | |
| II | አዲስ ደመወዝ | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 | 4929 |
| | ነባር ደመወዝ | 1338 | 1428 | 1523 | 1624 | 1731 | 1843 | 1958 | 2079 | 2208 | 2344 | 2487 |
| | | | | | | | | | | | | |
| III | አዲስ ደመወዝ | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 | 5104 |
| | ነባር ደመወዝ | 1624 | 1731 | 1843 | 1958 | 2079 | 2208 | 2344 | 2487 | 2638 | 2799 | 2969 |
| | | | | | | | | | | | | |
| IV | አዲስ ደመወዝ | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 | 5283 |
| | ነባር ደመወዝ | 1958 | 2079 | 2208 | 2344 | 2487 | 2638 | 2799 | 2969 | 3150 | 3333 | 3526 |
| | | | | | | | | | | | | |
| V | አዲስ ደመወዝ | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 | 5659 |
| | ነባር ደመወዝ | 2344 | 2487 | 2638 | 2799 | 2969 | 3150 | 3333 | 3526 | 3729 | 3934 | 4150 |
| | | | | | | | | | | | | |
| VI | አዲስ ደመወዝ | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 | 6058 |
| | ነባር ደመወዝ | 2799 | 2969 | 3150 | 3333 | 3526 | 3729 | 3934 | 4150 | 4379 | 4609 | 4851 |
| | | | | | | | | | | | | |
| VII | አዲስ ደመወዝ | 6485 | 6485 | 6485 | 6485 | 6485 | 6485 | 6485 | 6485 | 6485 | 6485 | 6709 |
| | ነባር ደመወዝ | 3333 | 3526 | 3729 | 3934 | 4150 | 4379 | 4609 | 4851 | 5098 | 5358 | 5626 |
| | | | | | | | | | | | | |
| VIII | አዲስ ደመወዝ | 6940 | 6940 | 6940 | 6940 | 6940 | 6940 | 6940 | 6940 | 6940 | 7424 | 7676 |
| | ነባር ደመወዝ | 3934 | 4150 | 4379 | 4609 | 4851 | 5098 | 5358 | 5626 | 5907 | 6193 | 6481 |

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

| ደረጃ | መግለጫ | መነሻ ደመወዝ | የእርከን ደመወዝ | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| IX | አዲስ ደመወዝ | 7424 | 7424 | 7424 | 7424 | 7424 | 7424 | 7424 | 7676 | 7934 | 8199 | 8474 |
| | ነባር ደመወዝ | 4609 | 4851 | 5098 | 5358 | 5626 | 5907 | 6193 | 6481 | 6773 | 7071 | 7377 |
| X | አዲስ ደመወዝ | 7934 | 7934 | 7934 | 7934 | 7934 | 7934 | 8474 | 8758 | 9047 | 9341 | 9645 |
| | ነባር ደመወዝ | 5358 | 5626 | 5907 | 6193 | 6481 | 6773 | 7071 | 7377 | 7690 | 8017 | 8354 |
| XI | አዲስ ደመወዝ | 8474 | 8474 | 8474 | 8474 | 8758 | 9047 | 9341 | 9645 | 9953 | 10272 | 10600 |
| | ነባር ደመወዝ | 6193 | 6481 | 6773 | 7071 | 7377 | 7690 | 8017 | 8354 | 8705 | 9056 | 9420 |
| XII | አዲስ ደመወዝ | 9047 | 9047 | 9047 | 9341 | 9645 | 9953 | 10272 | 10600 | 10934 | 11279 | 11634 |
| | ነባር ደመወዝ | 7071 | 7377 | 7690 | 8017 | 8354 | 8705 | 9056 | 9420 | 9785 | 10150 | 10521 |
| XIII | አዲስ ደመወዝ | 9645 | 9645 | 9953 | 10272 | 10600 | 10934 | 11279 | 11634 | 12001 | 12379 | 12765 |
| | ነባር ደመወዝ | 8017 | 8354 | 8705 | 9056 | 9420 | 9785 | 10150 | 10521 | 10906 | 11305 | 11719 |
| XIV | አዲስ ደመወዝ | 10600 | 10600 | 10934 | 11279 | 11634 | 12001 | 12379 | 12765 | 13163 | 13998 | 14432 |
| | ነባር ደመወዝ | 9056 | 9420 | 9785 | 10150 | 10521 | 10906 | 11305 | 11719 | 12148 | 12579 | 13013 |
| XV | አዲስ ደመወዝ | 11634 | 11634 | 12001 | 12379 | 12765 | 13163 | 13998 | 14432 | 14879 | 15340 | 15802 |
| | ነባር ደመወዝ | 10150 | 10521 | 10906 | 11305 | 11719 | 12148 | 12579 | 13013 | 13462 | 13926 | 14400 |
| XVI | አዲስ ደመወዝ | 12765 | 12765 | 13163 | 13998 | 14432 | 14879 | 15340 | 15802 | 16267 | 16738 | 16738 |
| | ነባር ደመወዝ | 11305 | 11719 | 12148 | 12579 | 13013 | 13462 | 13926 | 14400 | 14890 | 15396 | 15912 |
| XVII | አዲስ ደመወዝ | 13998 | 14432 | 14879 | 15340 | 15802 | 16267 | 16738 | 17220 | 17716 | 18226 | 18751 |
| | ነባር ደመወዝ | 12579 | 13013 | 13462 | 13926 | 14400 | 14890 | 15396 | 15912 | 16437 | 16979 | 17531 |
| XVIII | አዲስ ደመወዝ | 15340 | 15802 | 16267 | 16738 | 17220 | 17716 | 18226 | 18751 | 19291 | 19820 | 20363 |
| | ነባር ደመወዝ | 13926 | 14400 | 14890 | 15396 | 15912 | 16437 | 16979 | 17531 | 18092 | 18671 | 19252 |

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

| ደረጃ | መግለጫ | መነሻ ደመወዝ | የእርከን ደመወዝ | | | | | | | | | ጣሪያ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | |
| | | | | | | | | | | | | |
| XIX | አዲስ ደመወዝ | 16738 | 17220 | 17716 | 18226 | 18751 | 19291 | 19820 | 20363 | 20921 | 21491 | 22072 |
| | ነባር ደመወዝ | 15396 | 15912 | 16437 | 16979 | 17531 | 18092 | 18671 | 19252 | 19850 | 20468 | 21092 |
| | | | | | | | | | | | | |
| XX | አዲስ ደመወዝ | 18226 | 18751 | 19291 | 19820 | 20363 | 20921 | 21491 | 22079 | 22682 | 23301 | 23937 |
| | ነባር ደመወዝ | 16979 | 17531 | 18092 | 18671 | 19252 | 19850 | 20468 | 21092 | 21725 | 22361 | 23005 |
| | | | | | | | | | | | | |
| XXI | አዲስ ደመወዝ | 19820 | 20363 | 20921 | 21491 | 22079 | 22682 | 23301 | 23937 | 24583 | 25235 | 25904 |
| | ነባር ደመወዝ | 18671 | 19252 | 19850 | 20468 | 21092 | 21725 | 22361 | 23005 | 23654 | 24305 | 24961 |
| | | | | | | | | | | | | |
| XXII | አዲስ ደመወዝ | 21491 | 22079 | 22682 | 23301 | 23937 | 24583 | 25235 | 25904 | | | |
| | ነባር ደመወዝ | 20468 | 21092 | 21725 | 22361 | 23005 | 23654 | 24305 | 24961 | | | |

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚ...ር

የገንዘብ ሚኒስቴር
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት 2

Civil Service Commission

ፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
Federal Civil Service Commission

# የኑሮ ውድነት ማካካሻ የደመወዝ ማስተካከያ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 1029/2017

ጥቅምት 2017ዓ.ም

አዲስ አበባ

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ

## 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች "የኑሮ ውድነት ማካካሻ የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ መመሪያ ቁጥር 1029/2017" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## 2. ትርጓሜ

1) «የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ» ማለት የአንድን ሠራተኛ ደመወዝ ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል ለማሸጋገር ሲባል ቅርበቱ እየታየ የነበረውን ደመወዝ እንደሁኔታው ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል የመነሻ፣ የእርከን ወይም የጣሪያ ደመወዝ ላይ ለማሳረፍ የሚፈቅድ የደመወዝ ማስተካከያ ነው፡፡

2) «ኮሚሽን» ማለት የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ነው፡፡

## 3. የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸ የሴት ጾታንም ያካትታል፡፡

# ክፍል ሁለት

## 4. በሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ የተሰጠባቸው ጉዳዮች

1) የደመወዝ ማስተካከያ ክፍያው በፌደራልም ሆነ በክልል ደረጃ ክፍያው ከጥቅምት 1 ቀን 2017ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

2) ለልዩ ደመወዝ ስኬል ተጠቃሚዎች የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን የመንግስት ሠራተኞችን የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ መጠን መሠረት በማድረግ የደመወዝ ስኬል ማሻሻያ እና የመሸጋገሪያ ሠንጠረዥ አዘጋጅቶ ያስተላልፋል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

3) የተደረገው የደመወዝ ማስተካከያ ከፍተኛ ወጪ የሚያስከትል በመሆኑ በዚህ የበጀት ዓመት በየትኛውም ደረጃ ባሉ የመንግሥት ተቋማት ምንም ዓይነት የደመወዝ ስኬል ማሻሻያም ሆነ የጥቅማ-ጥቅም ጥያቄ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት አቅጣጫ ካልተሰጠ በስተቀር አይስተናገድም፡፡

4) ዳኞች፣ አቃቤያነ ህግ እና ወርሃዊ ደመወዛቸው ብር 25,000 እና በላይ የሆናቸው የመንግስት ሠራተኞች፣ ተሿሚዎች እና የህዝብ ተመራጮች በዚህ ጥናት ያልተካተቱ በመሆኑ ይህ መመሪያ ተፈጻሚ አይሆንባቸውም፡፡

## ክፍል ሶስት
## ዝርዝር አፈጻጸም

5. የኑሮ ውድነት ማካካሻ የደመወዝ ማስተካከያን በሚመለከት መንግሥት ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀው የአፈጻጸም መመሪያ ከዚህ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

1) በዚህ የኑሮ ውድነት ማካካሻ ተጠቃሚ የሚሆኑ ሠራተኞች ባገኙት የደመወዝ ማስተካከያ ምክንያት፡-

ሀ) የመደበኛ የደመወዝ ጭማሪ ኡደታቸው አይለወጥም፡፡

ለ) ለደረጃ እድገት የአንድ ዓመት መቆያ ጊዜ ማሟላት አይጠበቅባቸውም፡፡

2) ከፍ ባለ የሥራ ደረጃ ላይ በተጠባባቂነት የተመደበ ሠራተኛ የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ ልዩነት የሚታሰብለት በድልድሉ በተመደበበት ደረጃ ላይ ነው፡፡

3) በሀምሌ ወር 2011 ዓ.ም ተሻሽሎ በሥራ ላይ በዋለው ወይም አግባብ ባለው አካል በተፈቀደ የደመወዝ ስኬል ጣሪያ ላይ የደረሰና በአዲሱ የደመወዝ ስኬል ጣሪያው የሚነሳለት ሠራተኛ በተመደበበት የሥራ ደረጃ የአዲሱን የደመወዝ ስኬል ጣሪያ ሳያልፍ ማስተካከያውን እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡



መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

4) ኮሚሽኑ በአንድ ተቋም ከተፈጸሙ የሠራተኞች ድልድል ወይም የደረጃ እድገት መካከል በተለያዩ ሕግን ባልተከተሉ አሠራሮች ምክንያት ያልተቀበለው ካለ የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ ጭማሪው የሚሰጠው በድልድል አፈጻጸም መመሪያው መሠረት ሠራተኛው በሚያሟላበት ደረጃ ከተደለደለ በኋላ ነው፡፡

5) ከፍ ካለ የሥራ ደረጃ ላይ በሚታሰብ ደመወዝ ተቀጥሮ እየተቀነሰ የሚከፈለው ሠራተኛ የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ ተጠቃሚ የሚሆነው በሚያሟላበት ደረጃ ላይ ተመሥርቶ ይሆናል፡፡

6) በሙከራ ቅጥር ላይ የሚገኝ ሠራተኛ የዚህ የደመወዝ ስኬል መሸጋገሪያ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

7) በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያት ከደረጃው ዝቅ ያለና ደመወዙ የተቀነሰበት ሠራተኛ ማስተካከያው የሚሰጠው በተቀነሰው ደረጃና ደመወዝ ላይ ታስቦ ነው፡፡ ሆኖም በተወሰነ የጊዜ ገደብ ከደረጃና ደመወዝ ዝቅ የተደረገ ሠራተኛ የጊዜ ገደቡ ደርሶ ወደ ቀድሞ ደረጃው ሲመለስ ከተመለሰበት ጊዜ ጀምሮ በአዲሱ የደመወዝ ስኬል ተገቢው ደመወዝ ይሰጠዋል፡፡

8) ያለደመወዝ ልዩ ፈቃድ ተሰጥቶት በፕሮጀክት አፈፃፀም መመሪያ መሠረት ወደ ፕሮጀክት የተዛወረ ወይም በፕሮጀክት የተቀጠረ ሠራተኛ ወደ መደበኛ ሥራው ሲመለስ ወደ ፕሮጀክት ከመዛወሩ በፊት በነበረበት የሥራ መደብ /ደረጃ/ የተወሰነው አዲሱ ደመወዝ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

9) ይህ የደመወዝ ስኬል ማስተካከያ ጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ወይም የፕሮጀክት ሠራተኞችን ይመለከታል፡፡ በኮሚሽኑ ተመዝኖ ደረጃ በወጣለት ወይም በቋሚ የሥራ መደብ ላይ መመሪያውን ተከትሎ የተቀጠረ ጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ሠራተኛ ወይም በሚመለከተው አካል በተፈቀደ የፕሮጀክት ደመወዝ ወይም ልዩ የደመወዝ ስኬል የተቀጠረ ጊዜያዊ ወይም የኮንትራት ሠራተኛ የደመወዝ ማስተካከያ ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

10) በተለያዩ ምክንያቶች ከመደበኛ ሥራው ተለይቶ የቆየ ሠራተኛ ወደ ሥራው እንዲመለስ ሲደረግ ተመዝኖ ደረጃ በወጣለት የሥራ መደብ ላይ እንዲመደብ ከተደረገ በኋላ ደመወዙ ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡

11) በሥራው ልዩ ባህርይ ምክንያት እያስተማረ የህክምና አገልግሎት የሚያበረክት የጤና ባለሙያ የማስተማር ሥራው እንደተጠበቀ ሆኖ በአካዳሚክ ወይም በጤና ሙያ /ከፍ ባለው/ ደረጃ ላይ ብቻ ማስተካከያው ይከፈለዋል፡፡

12) ይህ የደመወዝ ስኬል ሥራ ላይ ሲውል የአንድ ሠራተኛ ደመወዝ፡-

12.1. ከተመደበበት ደረጃ የመነሻ ደመወዝ በታች ከሆነ ወደ መነሻ ደመወዝ ከፍ እንዲል ይደረጋል፡፡

12.2. ከመነሻው ደመወዝ በላይ ሆኖ በእርከን ደመወዝ ላይ የማያርፍ ከሆነ ወደ ሚቀጥለው የእርከን ደመወዝ ከፍ እንዲል ይደረጋል።

12.3. ከስኬሉ የመነሻ፣ የእርከን ወይም የጣሪያ ደመወዝ ጋር ከገጠመ ወይም ከጣሪያው በላይ ከሆነ የደመወዝ ማስተካከያ ጭማሪ አይደረግም፡፡

13) በአደረጃጀት ለውጥ ምክንያት በትርፍነት ተይዘው በመንግሥት ሠራተኞች የድልድል አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 859/2014 መሠረት ወደ ሌላ መሥሪያ ቤት እስኪመደቡ ደመወዝ እየተከፈላቸው ያሉ ደመወዛቸው ወደ አዲሱ የደመወዝ ስኬል እንዲሸጋገር ይደረጋል፡፡

14) አግባብ ባለው አካል ባልተፈቀደ ልዩ የደመወዝ ስኬል እና በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ተመዝኖ ደረጃ ባልወጣለት የሥራ መደብ ላይ የደመወዝ ማስተካከያ መፈጸም በጥብቅ የተከለከለ ነው፡፡

15) በማንኛውም ህጋዊ ምክንያት ከነበረበት የሥራ ደረጃና ደመወዝ ዝቅ ተደረገ ሠራተኛ የደመወዝ ማስተካከያው ዝቅ ባለው የሥራ ደረጃ ይሠራለታል፡፡

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር

16)ከጥቅምት 2017 ዓ.ም ጀምሮ በነባሩ የደመወዝ ስኬል የሠራተኛ ስምሪት መፈጸም አይቻልም፡፡

17)ልዩ የደመወዝ ስኬል የተፈቀደላቸው ተቋማት ከብር 25,000 በታች ላሉ የመነሻ፣ የእርከን ወይም የጣሪያ ደመወዞች የደመወዝ ማስተካከያ የተደረገ ሲሆን፣ ብር 25,000 እና በላይ የነበሩ ደመወዞች በደመወዝ ስኬሉ ላይ እንደነበሩ የሚቀጥሉ ይሆናል፡፡

18)አንድ ተሿሚ እየተከፈለው ያለው የወር ደመወዝ በሚያርፍበት ምድብ ካሉ ሌሎች ደመወዞች ጋር ካልገጠመ ሊከፈለው የሚገባው የደመወዝ መጠን ለኮሚሽኑ ቀርቦ ይወሰናል፡፡

## 6. ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## 7. ተጠያቂነት

የዚህ መመሪያን ድንጋጌዎች በመተላለፍ፣ በመመሪያው ከተመለከተው ሥርዓት ውጭ የኑሮ ውድነት ማካካሻ ክፍያ የሚፈጽም ኃላፊ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## 8. በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች

በዚህ መመሪያ ያልተሸፈኑ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ ጥያቄው ለኮሚሽኑ እየቀረበ ውሳኔ የሚሰጥበት ይሆናል፡፡

## 9. መመሪያውን ስለማሻሻል

በሥራ ላይ የሚያጋጥሙ ችግሮችንና ክፍተቶችን ለመፍታት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝ ኮሚሽኑ የማስፈጸሚያ መመሪያውን ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 10. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጸድቆ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበና በተቋሙ ድረገጽ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

---------------------

መኩሪያ ኃይሌ (ፒ.ኤች.ዲ)
ኮሚሽነር